**የቋንቋ ተደራሽነት የደምበኛ አማካሪ ቡድን** ትብብር የሚያደርግ አካል ሲሆን የተወሰነ የእንግሊዘኛ ችሎታ ያላቸው (ኤል.ኢ.ፒ) እና የእንግሊዘኛ ችሎታ የሌላቸው (ኤን.ኢ.ፒ) የሰብዓዊ አገልግሎቶች መምሪያ (ዲ.ኤች.ኤስ) ደምበኞች እና ከዲ.ኤች.ኤስ ጋር ግንኙነት ከሚፈጥሩ ባለ ድርሻ አካላት የተውጣጣ ነው። ተግባሩም የኤል.ኢ.ፒ እና ኤን.ኢ.ፒ ደምበኞችን ቆይታ ለማሻሻል በሚያስችሉ ስትራቴጂዎች ላይ በሚከተሉት ዙሪያ ማማከር ነው፥

- የቋንቋ ተደራሽነትን በተመለከተ ከዲ.ኤች.ኤስ አገልግሎት ማዕከላት ወይም ሌሎች የዲ.ኤች.ኤስ አገልግሎቶች የቀረቡ ምልከታዎች፣ አስቸጋሪ ነገሮች፣ ወይም አሳሳቢ ነገሮች ዙሪያ ምክር መስጠት።
- የቋንቋ ተደራሽነት አገልግሎቶችን ለማሻሻል ለዲ.ኤች.ኤስ ምክረ ሃሳቦችን መስጠት።
- ከቋንቋ ተደራሽነት ጋር በተያያዘ የኤጀንሲ መመሪያዎችን በማዘጋጀት ረገድ ድጋፍ መስጠት።

## ስብሰባዎቹ የሚደረጉበት ወቅት/ ቦታዎች

አማካሪ ቡድኑ በየእሩብ ዓመቱ አንድ ጊዜ ለቡድን አባላቱ በጣም አመቺ በሆኑ ጊዜያት እና ቦታዎች ይገናኛል/ይሰበሰባል።

## እንዴት መሳተፍ ይችላሉ?

ማንኛውም አይነት ጥያቄ ካለዎት ወይም የቋንቋ ተደራሽነት የደምበኛ አማካሪ ቡድንን መቀላቀል ከፈለጉ የዲ.ኤች.ኤስ የቋንቋ ተደራሽነት አስተባባሪ የሆነውን ጄሚ ሆልጉንን በ jaime.holguin@dc.gov ወይም (202)671.4731 ያነጋግሩ።